# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተሸከርካሪ ከመንገድ ሊነሳ የሚችልበት አሠራርን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 41/2013

Directive Issued by the Addis Ababa City Administration to Determine the Procedure for Removing a Vehicle from the Road (Directive No. 41/2013)

የአዲስ አበባ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት ባለስልጣን
Addis Ababa City Traffic Management Authority

መጋቢት 21፥ 2012

## መግቢያ

በአዲስ አበባ ከተማ የትራፊክ እንቅስቃሴን በመግታት በተለያዩ ህጋዊ ባልሆኑ ምክንያቶች ተሽከርካሪዎችን በማቆም የትራፊክ እንቅስቃሴ መስተጓጎልን ለመቆጣጠር የአፈፃፀም መመሪያ ማውጣት በማስፈለጉ፣

ተሽከርካሪዎች የሚነሱበትን አግባብ፣ ሲነሱ ሊወሰድ የሚገባውን ጥንቃቄ እና የተነሱ ተሽከርካሪዎች ሊመለሱ የሚችሉበትን አሰራር በህግ መወሰን አስፈላጊ በመሆኑ፣

የአዲስ አበባ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈፃሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀትና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 64/2011 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀፅ 3 (ሠ) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተሽከርካሪ ከመንገድ ሊነሳ የሚችልበት አሠራርን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር** 41/2013 **ዓ.ም**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ፡-

1. **“ቢሮ”** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ ነው፤
2. **“ከተማ”** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤
3. **“ትራፊክ ተቆጣጣሪ”** ማለት የትራፊክ እና የትራንስፖርት ህጎችን ለማስፈጸም አግባብነት ባለው ህግ ስልጣን የተሰጠው ሰው ወይም ትራፊክ ፖሊስ ወይም የትራንስፖርት ተቆጣጣሪ ነው፤
4. **“ተሽከርካሪ ”**ማለት በመካኒካል ወይም በኤሌክትሪክ ኃይል እየተንቀሳቀሰ የሚኔድ ማንኛውም ተሽከርካሪ ሆኖ ከዋናው መኪና ተገንጥለው ወይም ተቆርጠው በመንገድ ላይ የቆሙ የተሽከርካሪ አካላትን ይጨምራል፡፡

5. **"ደንብ"** ማለት የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክን ለመቆጣጠር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 208/2003 በደንብ ቁጥር 395/2009 እንደተሻሻለ ነው፡፡
6. **"መንገድ"** ማለት በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ የሚገኝና በከተማ አስተዳደሩ የሚተዳደር ለማንኛውም ተላላፊ ትራፊክ ክፍት ካልሆነ የግል መንገድ በስተቀር ዋና መንገድ፣ መለስተኛ መንገድ፣ መጋቢ መንገድ፣ የውስጥ ለውስጥ መንገድ፣ የመንደር መንገድ፣ አደባባይ እና የአደባባይ ዙሪያ፣ የመንገድ አካፋይ ደሴት ነው፡፡
7. **"የእግረኛ መንገድ"** ማለት ተሽከርካሪዎች እንዲንቀሳቀስበት የተዘጋጀውን መንገድ ጠርዝ ተከትሎ ወይም ለብቻው ለእግረኛ እንቅስቃሴ የሚውል መንገድ ነው፡፡
8. **"ተሽከርካሪን ማንሳት"** ማለት በብልሽት፣ በአደጋ፣ የትራፊክ ፍሰቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ በሚያሳድር መልኩ የቆመን ተሽከርካሪ በማንሳትና በሌላ ተሽከርካሪ ላይ በመጫን ወይም በመጎተት መንገዱን ለትራፊክ ፍሰት ክፍት የማድረግ አገልግሎት ነው፡፡
9. **"ሶስተኛ ወገኖች"** ማለት ከኤጀንሲው ጋር የክሬን አገልግሎት ውል በመግባት ተሽከርካሪን ከመንገድ ለማንሳት የሚሰማሩ የክሬን አቅራቢ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ናቸው፡፡
10. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካልነው፡፡

**3. የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኙ መንገዶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**4. የጾታ አገላለፅ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ልዩ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀ አነጋገር ለሴትም ፆታ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለትራፊክ ተቆጣጣሪ እና ተሽከርካሪን ከመንገድ ስለማንሳት

**5. ስለትራፊክ ተቆጣጣሪ**

1. ማንኛውም ትራፊክ ተቆጣጣሪ በደንቡ እና በዚህ መመሪያ ከተደነገገው ውጪ ተሽከርካሪን ከመንገድ ማንሳት የተከለከለ ነው፡፡
2. ከመንገድ ለተነሳ ተሽከርካሪ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡

## 6. ተሽከርካሪ ከመንገድ የሚነሳባቸው ምክንያቶች

### 1. የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ህግ ሲተላለፍ

የመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪ ህግ መተላለፍ ጥፋቶች ተፈፅመው ሲገኙ ማንኛውም ተሽከርካሪ ከታች በተገለጸው ምክንያቶች ከመንገድ እንዲነሳ ሊደረግ ይችላል፡፡

ሀ) በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀፅ 31 መሠረት ተሽከርካሪን ለጊዜው ወይም ለረጅም ጊዜ ማቆም በተከለከለባቸው ሥፍራዎች ማቆምና በትራፊክ ተቆጣጣሪ እንዲነሳ ሲታዘዝ ፈቃደኛ አለመሆን ወይም በስፍራዉ አለመገኘት፤

ለ) የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ በሌለው ሰው ሲሽከረከር የተያዘተ ሽከርካሪ ተሽከርካሪውን ሲያሽከረክር የነበረው ግለሰብ ወዲያውኑ ተሽከርካሪውን ለማሽከርከር የሚያስችል ፍቃድ ያለውን ሰው ማቅረብና ተሽከርካሪውን ማንሳት ካልቻለ፤

ሐ) አደንዛዥ ዕፅ ወስዶ ወይም በአልኮል መጠጥ ሰክሮ የተገኘ አሽከርካሪ ሌላ ሰው ተሽከርካሪውን እንዲያሽከረክርለት ማድረግ ካልቻለ፤

መ) ዓመታዊ ምርመራ ተደርጎለት የቴክኒክ ብቃቱ ያልተረጋገጠ ተሽከርካሪ ወይም በሚመለከተው አካል በድንገተኛ ምርመራ የቴክኒክ ብቃቱን እንደማያሟላ የተረጋገጠ ተሽከርካሪ፤

ሠ) የፊትና የኃላ ታርጋ የሌለው ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ ሲሽከረከር ከተገኘ፤

ረ) በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀፅ 32 ላይ የተቀመጠውን በመተላለፍ በመንገድ ላይ ቆሞ የተገኘ ተሽከርካሪ፤

ሸ) ሦስተኛ ወገን ኢንሹራንስ መግባቱን የሚያሳይ ምልክት በተሽከርካሪው ላይ ሳይለጥፍ የተገኘ ተሽከርካሪ፤

ቀ) ከአሠራሩ፣ ከአያያዙ ወይም ከአቀማመጡ ጉድለት የተነሳ በጎማዎቹ ወይም ጎማዎቹን በሚያሽከረክሩ ክብ ነገሮች ወይም ኩሽኔታዎች ወይም በሌላው የአካል

ክፍል መንገዱን ለማበላሸት የሚችል ተሽከርካሪ በመንገድ ላይ ሲሽከረከር ከተገኘ፤

በ) በከባድ ጭነት ተሽከርካሪዎች መንቀሳቀሻ ፈቃድ መመሪያ ለከባድ ጭነት ተሽከርካሪዎች በተከለከለ ሰአት ቦታ ላይ ማቆምና በትራፊክ ተቆጣጣሪ እንዲነሳ ሲታዘዝ ፈቃደኛ አለመሆን ወይም በስፍራዉ አለመገኘት፤

## 2. ተሽከርካሪው በብልበሽት ወይም በግጭት ሲቆም

ተሽከራካሪ በብልሽት ወይም በግጭት የቆመ ተሽከርካሪን በሚከተሉት ምክንያቶች ከመንገድ ማንሳት ይቻላል፡-

1. አንድ ተሽከርካሪ በግጭት ወይም በመገልበጥ ወይም በብልሽት ምክንያት መንገድ ዘግቶ ከተገኘ ወይም የትራፊክ ፍሰቱን ካሰናከለ የተሽከርካሪው ባለንብረት ወይም አሽከርካሪው ተሽከርካሪውን ወዲያውኑ ማንሳት ካልቻለ ወይም በስፍራው ካልተገኘ፤
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ተሽከርካሪውን ለማንቀሳቀስ ወይም ካለበት ቦታ ለማንሳት ያህል የሚያስፈልገውን የመጠገን ሥራ የመንገዱን ጠርዝ በመያዝ ለመስራት በሚችልበት ጊዜ በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀፅ 9 ንዑስ ቁጥር 2 (ለ) ላይ ከተጠቀሰው ጊዜ በላይ በመንገድ ላይ ያለመቋረጥ ቆሞ ሲገኝ፤
3. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ ቢኖርም ተቆጣጠሪው መስሪያቤት የጥገና ስራው በመንገዱ ለሚጠቀሙት ሌሎች ተላላፊዎች እንቅፋት ከሆነ ከላይ የተጠቀሰውን ጊዜ መጠበቅ ሳያስፈልግ ተሽከርካሪው ከመንገድ እንዲነሳ ሊደረግ ይችላል፡፡

## 3. ተሽከርካሪዎች ፍሰትን በማስተጓጉል ሲቆም

ትራፊክ ተቆጣጣሪው ተሽከርካሪው በመንገድ ላይ በመቆሙ ተላላፊዎችን የሚያሰናክል ሆኖ ሲያገኘውና የተሽከርካሪው መነሳት ችግሩን ለማስቀረት አስፈላጊ መስሎ ሲታየው ተሽከርካሪው እንዲነሳ አሽከርካሪውን ወይም በኃላፊነት የተረከበውን

ሰው አዞ ትዕዛዙን ለመፈፀም ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም በስፍራው ካልተገኘ ተሽከርካሪው ሊነሳ ይችላል፡፡

4. **ለረጅም ጊዜ በመንገድ ላይ ስለቆሙ ተሽከርካሪዎች**

በመንገድ ትራንስፖርት ትራፊክ መቆጣጠሪያ ደንብ ቁጥር 208/2003 አንቀፅ 9 ንዑስ ቁጥር 2 (ለ) ላይ ከተጠቀሰው ጊዜ በላይ በመንገድ ላይ ያለመቋረጥ መቆማቸው የተረጋገጡ ተሽከርካሪዎችበሚሰጣቸው ማስጠንቀቂያ መሠረት ተሽከርካሪውን ከመንገድ ላይ ለማንሳት ካልቻሉ ተሽከርካሪውእንዲነሳ ለማድረግ ይቻላል፡፡

5. **ተሽከርካሪ ከመንገድ ሊነሳባቸው የሚችልባቸው ሌሎች ሁኔታዎች**

ከመንገድ ውጪ እና የትራፊክ ፍሰትን በማይነካ መልኩ አደጋ ሲደርስና አደጋው በሰዎች ህይወትና አካል ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ በአግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ እንዲነሳ ሊደረግ ይችላል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ተሽከርካሪን በሶስተኛ ወገኖች ስለሚነሳበት ሁኔታ

7. **በኤጀንሲው ስለሚከናወኑ ተግባራት**

1. ኤጀንሲው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከዚህ በላይ ባሉ ድንጋጌዎች መሠረት ከመንገድ የሚነሱ ተሽከርካሪዎች ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርገው የውል ስምምነት መሠረት እንዲነሱ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በሶስተኛ ወገኖች አማካኝነት ተሽከርካሪዎች ከመንገድ ለማንሳት የሚፈፀሙ የአገልግሎት ግዥዎች በመንግስት የግዥ ስርዓት መሠረት የሚፈፀሙ ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ መሠረት በሶስተኛ ወገኖች አማካኝነት ተሽከርካሪን ከመንገድ ለማንሳት በአንድ ጊዜ ግዥ የሚፈፀሙ የአገልግሎች ውሎች ቆይታ ከሁለት ዓመት መብለጥ የለበትም፡፡

8. **ተሽከርካሪ በሶስተኛ ወገኖች እንዲነሳ ስለማድረግ**

1. ከኤጀንሲው ጋር ውል የገቡ ሶስተኛ ወገኖች ኤጀንሲው በሚያሰማራቸው አካባቢዎች ተሽከርካሪዎችን ከመንገድ ሊያነሱ ይችላሉ፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በሶስተኛ ወገኖች አማካኝነት ተሽከርካሪ ከመንገድ የሚነሳው በኤጀንሲው ውሳኔ እና የኤጀንሲው ተቆጣጣሪዎች ባሉበት መሆን አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## የትራፊክ ተቆጣጣሪ ተግባርና ኃላፊነት

### 9. ትዕዛዝና ማስጠንቀቂያ ስለመስጠት

#### 1. ትዕዛዝ የመስጠት ግዴታ

ሀ. የትራፊክ ተቆጣጣሪ ተሽከርካሪው በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6, ንኡስ አንቀጽ 1፣ 2 እና 3 መሠረት ተሽከርካሪ እንዲነሳ ከማድረጉ በፊት ለአሽከርካሪው ወይም ተሽከርካሪውን በኃላፊነት ለተቀበለው ሰው ተሽከርካሪውን በአስቸኳይ እንዲያነሳ ትዕዛዝ መስጠት አለበት፡፡

ለ. የተሽከርካሪው አሽከርካሪ ወይም ተሽከርካሪውን በኃላፊነት የተቀበለው ሰው በስፍራው በማይኖርበት ጊዜ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 (ሀ) የተቀመጠው ግዴታ በትራፊክ ተቆጣጣሪው ላይ አይኖርም፡፡

#### 2. ተሽከርካሪ እንዲነሳ ማስጠንቀቂያ ስለመስጠት

1. አንድ ተሽከርካሪ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6(4) መሠረት በክሬን ከመነሳቱ በፊት የትራፊክ ተቆጣጣሪ ተሽከርካሪው እንዲነሳ ማስጠንቀቂያ መስጠት አለበት፡፡
2. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6(4) መሠረት ንብረቱ እንዲነሳ ከመወሰኑ በፊት ንብረቱ በ5 ቀናት ውስጥ ከመንገድ እንዲነሳ የሚያሳስብ ማስጠንቀቂያ ስቲከር ይለጠፍበታል፡፡
3. በዚህ በአንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የሚለጠፈው ማስጠንቀቂያ ቢያንስ የሚከተለውን መያዝ አለበት፡-

ሀ. የተሽከርካሪውን ሰሌዳ ቁጥር ( ካለው)፣

ለ. ማስጠንቀቂያው የተለጠፈበት ቀንና ሰዓት፣

ሐ. ተሽከርካሪው መነሳት ያለበትን ጊዜ፣

መ.ተሽከርካሪው በማስጠንቀቂያው በተገለፀው ጊዜ ካልተነሳ ኤጀንሲው በክሬን እንዲነሳ እንደሚያደረግና ለዚሁ የወጣውን ወጪም በተሽከርካሪው ባለቤት እንደሚሸፍን፣

## 10.መረጃ የመስጠት ግዴታ

1. የትራፊክ ተቆጣጣሪ የተነሳው ተሽከርካሪን መረጃ እና ተሽከርካሪው ወደየት እንደተወሰደ በአካባቢው ላለ ፖሊስ ጣቢያ ወይም የማህበረሰብ አቀፍ ፖሊስ ማሳወቅ አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ቢኖርም ተሽከርካሪው የተነሳው አሽከርካሪው ወይም በኃላፊነት የተቀበለው ሰው ባለበት ከሆነ ለተሽከርካሪው ባለቤት ከማሳወቅ ባለፈ ትራፊክ ተቆጣጣሪው በንዑስ አንቀፅ 1 የተገለፀው ግዴታ አይኖርበትም፡፡
3. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የተሽከርካሪ አሽከርካሪ ወይም በኃላፊነት የተቀበለው ሰው ተሽከርካሪው ሲነሳ በቦታው ስለመኖሩ በተዘጋጀው ቅፅ ላይ እንዲፈርም መደረግ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3 መሠረት እንዲፈርም የተጠየቀ አሽከርካሪ ለመፈረም ፈቃደኛ ካልሆነ ፈቃደኛ አለመሆኑ በተዘጋጀው ቅፅ ላይ እንዲሰፍር መደረግ አለበት፡

## 11.ከትራፊክ ተቆጣጣሪ የሚጠበቅ ኃላፊነቶች

1. ተሽከርካሪ ከመንገድ እንዲነሳ የሚያደርግ የትራፊክ ተቆጣጣሪ ተሽከርካሪው ከመንገድ በሚነሳበት ወቅት/ጊዜ ተሽከርካሪዉ ላይ እና በራሱ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ተገቢዉን ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፤
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ ቢኖርም በዚህ መመሪያ መሰረት ከመንገድ እንዲነሳ የተደረገ ተሽከርካሪ ላይ በተቆጣጣሪው ከተነሳ በኃላ ለሚደርስ ማንኛውም አይነት ጉዳት ተሽከርካሪው ከመንገድ እንዲነሳ ያደረገው የትራፊክ ተቶጣጣሪ ተጠያቂ ሊሆን የሚችለው ጉዳቱ በትራፊክ ተቆጣጣሪው ግልፅ ጥፋት የደረሰ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

## 12.በአደጋ ምክንያት ለሚነሱ ተሽከርካሪዎች ስለሚደረግ ቅድመ ጥንቃቄ

ማንኛውም ተሽከርካሪ በአደጋ ምክንያት ከመነሳቱ በፊት ስለአደጋው የሚደረገው ምርመራ እንዲሁም የኢንሹራንስና ሌሎች ተያያዝ የህግ ጉዳዮች መጠናቀቃቸውን የትራፊክ ተቆጣጣሪው ማረጋገጥ አለበት፡፡

## ክፍል አምስት

## ከመንገድ የተነሳ ተሽከርካሪ ስለሚወሰድበት ስፍራ እና ስለሚለቀቅበት ሁኔታ

### 13.ከመንገድ የተነሳ ተሽከርካሪ ሊወሰድ ስለሚችልበት ሥፍራ

1. ኤጀንሲው ከመንገድ የሚነሱ ተሽከርካሪዎች የሚከማቹበት ደህንነቱ የተጠበቀ ስፍራ ማዘጋጀት አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ቢኖርም ማከማቻ ስፍራ እስኪዘጋጅ ድረስ በትራፊክ ተቆጣጣሪ የተነሳን ተሽከርካሪ ወደ ጋራዥ ወይም አደጋ ወደ ማያሰጋበት ሌላ ሥፍራ ለማዛወር የሚችል ሲሆን በተለይም ከዚህ በታች ወደ ተገለፁት ሥፍራዎች ሊወስድ ይችላል፡

   ሀ. የተነሱ ተሽከርካሪዎች እንዲቆሙበት የተዘጋጀ ሥፍራ፣

   ለ. አካባቢው ወዳለ ጋራዥ፣

   ሐ. አካባቢው ወዳለ ፖሊስ ጣቢያ፣ ሰላምና ጸጥታ አስተዳደር ጽህፈት ቤት ወይም ተገቢ ጥበቃ ወዳለው ሥፍራ፡፡

### 14.ተሽከርካሪውን መረከብ የሚችሉ አካላት

1. ተሽከርካሪው በአደጋ ወይም በብልሽት ምክንያት በመቆሙና በትራፊክ ተቆጣጣሪ እንዲያነሳ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ተሽከርካሪውን ባለማንሳቱ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 መሠረት የተነሳ ተሽከርካሪ ወይም በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1 (ሀ)፣, (ረ), እና (ሸ) መሠረት የተነሳ ተሽከርካሪ እንደአግባቡ በጊዜው ተሽከርካሪውን ሲያሽከረክር ለነበረ ሰው ወይም ለተሽከርካሪው ባለቤት ወይም ለህጋዊ ወኪል ይመለሳል፡፡
2. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1 (ለ) እና (ሐ) መሠረት የተነሳ ተሽከርካሪ በጊዜው ተሽከርካሪውን ሲያሽከረክር የነበረው ሰው ተሽከርካሪውን

ለማሽከርከር የሚያስችል የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ያለው ሰው ጋር በመሆን መረከብ ይችላል፡፡

3. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1 (ሐ) መሠረት የተነሳ ተሽከርካሪ ከአልኮል ወይም ከአደንዛዥ ዕፅ ተፅዕኖ ነፃ ሲሆን እራሱ መረከብ ይችላል፡፡
4. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1 (መ)፣ (ሠ) እና (ሸ) መሠረት የተነሳ ተሽከርካሪ በጊዜው ሲያሽከረክር የነበረ ግለሰብ ወይም የተሽከርካሪው ባለቤት ወይም ህጋዊ ወኪል ተሽከርካሪውን በማስጎተት ወይም ጭኖ ለማስወሰድ ይችላል፡፡
5. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 6 ንኡስ አንቀጽ 3 እና 4 መሠረት የሚነሳ ተሽከርካሪ ለመረከብ የሚችለው የተሽከርካሪው ባለቤት ወይም ህጋዊ ወኪሉ ነው፡፡

**15.ከመንገድ የተነሳ ተሽከርካሪ ለማስመለስ መሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ**

1. ከመንገድ የተነሳን ተሽከርካሪ ለመረከብ መብት ያለው ማንኛውም ሰው ተሽከርካሪውን ለመረከብ በሚቀርብበት ጊዜ የሚከተሉትን መረጃዎች እና ሁኔታዎች ማቅረብ አለበት

ሀ. ተሽከርካሪውን ለማንሳት እና ሌሎች ወጪዎች የወጣውን ወጪ መክፈሉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ

ለ. ባለንብረት ወይም ህጋዊ ወኪል ተሽከርካሪውን ለመረከብ በሚቀርብበት ጊዜ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነዶች እና የውክልና ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡

ሐ. በአንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1 (መ) ፣ (ሠ) እና (ሸ) መሠረት የተነሳ ተሽከርካሪ ተሽከርካሪውን በማስጎተት ወይም ጭኖ ለማስወሰድ የሚያስችል ተሽከርካሪ ማቅረብ አለባቸው፡፡

መ. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 (ሐ) ቢኖርም ተሽከርካሪው በተነሳበት ወቅት በተለያየ ምክንያት ሳይለጠፍ የቀረ ሦስተኛ ወገን መድህን መገባቱን የሚያሳይ ወይም ምርመራ መደረጉን የሚገልፅ ሰነድ ማቅረብ በቂ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>ስለክፍያ እና ቅጣት</u>

## 16.የመክፈል ግዴታ እና የክፍያ መጠን

1. ማንኛውም ተሽከርካሪው ከመንገድ የተነሳበት ሰው ተሽከርካሪውን ለማንሳት የወጣውን ወጪ ሙሉ በሙሉ የመሸፈን ግዴታ አለበት፡፡
2. ተሽከርካሪው ከመንገድ ከተነሳ በኃላ ለጥበቃ፣ ለማቆያ እና ሌሎች ለተሽከርካሪው ደህንነት የተወሰዱ እርምጃዎች ካሉ በአካባቢው የተሽከርካሪ ማቆሚያ የዋጋ ተመን መሠረት ተሽከርካሪውን ለመረከብ መብት ያለው ሰው መሸፈን አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 መሠረት የሚከፈለው ክፍያ መጠን ለክሬን የወጣውን የአገልግሎት ዋጋ ፣ተሽከርካሪው በሚነሳበት ወቅት ለተሳተፉ የፖሊስ እና ደንብ ማስከበር የትራንስፖርት አበል ፣ የሚነሳውን ተሽከርካሪ ክብደት ፣ ለሠራተኛ ጉልበት የሚወጣውን ወጪ፣ ተሽከርካሪው ተጎትቶ የሚሄድበትን ቦታ እርቀት፣ተሽከርካሪውን ለማንሳት የተለየ ሙያ በመጠየቁ ለዚሁ የወጣ ወጪ ካለ እንዲሁም ሌሎች ሁኔታዎች ከግምት በማስገባት ክፍያው የሚፈፀም ይሆናል፡፡
4. በዚህ አንቀፅ መሠረት የሚፈፀም ክፍያን የወቅቱን ገበያ መሠረት በማድረግ የሚወስን የክፍያ ገማች ኮሚቴ በኤጀንሲው እንዲቋቋም ይደረጋል፡፡

## 17.ቅጣት

አንድ ተሽከርካሪ በዚህ መመሪያ መሠረት ከመንገድ መነሳቱ በሌሎች ህጎች መሠረት የሚጣልበትን ቅጣት አያስቀርም፡፡

## ክፍል ሰባት

## ተሽከርካሪን የመረከቢያ ጊዜ እና ለመረከብ ስለመዘግየት

## 18.ተሽከርካሪን የመረከቢያ ጊዜ

1. ተሽከርካሪው በዚህ መመሪያ መሠረት የተነሳበት የተሽከርካሪ ባለቤት ወይም አሽከርካሪ ተሽከርካሪው እንደተነሳ ወይም መነሳቱን እንዳወቀ ወዲያውኑ ተሽከርካሪውን ለመረከብ ማሟላት ያለበትን ቅድመ ሁኔታዎች በማሟላት በማንኛውም የመንግስት የስራ ሰዓት መረከብ አለበት፡፡
2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ መሠረት የተነሳበትን ተሽከርካሪ ለመረከብ በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን ከሦስት ወር ጊዜ በላይ መቆየት የለበትም፡፡

**19.ከመረከብ ስለመዘግየት**

1. ማንኛውም ሰው በዚህ መመሪያ መሠረት የተነሳበትን ተሽከርካሪ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 18 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ካልተረከበ ከመረከብ እንደዘገየ ይቆጠራል፡፡
2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ተሽከርካሪው ካልተረከበ አግባብ ባላቸው ህጎች መሠረት ቀጣይ እርምጃ እንዲወሰድ ይደረጋል፡፡

## ክፍል ስምንት

## ስለ ቅሬታ አፈታት

**20.ቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት**

1. በዚህ መመሪያ መሠረት በትራፊክ ተቆጣጣሪው የተሰጠ ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው በ48 ሰዓት ውሰጥ ቅሬታውን ለትራፊክ ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቱ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. የትራፊክ ተቆጣጣሪ መስሪያ ቤቱ ቅሬታው በቀረበለት በ 5 የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡
3. የኤጀንሲው ውሳኔ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ሲሆን በ10 ቀናት ውስጥ አግባብ ካለው አካል ተለዋጭ ትዕዛዝ ካልመጣ በስተቀር ተሽከርካሪውን ለማንሳት የወጣውን እና ተያያዥ ወጪዎች የመሸፈን ግዴታ አለበት፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**21.የመተባበር ግዴታ**

ይህ መመሪያ በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ማንኛውም ሰው አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ አለባቸው፡፡

**22.ተፈፃሚነት የማይኖራቸዉ ህጎች**

በዚህ መመሪያ ዉስጥ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የሚቃረን መመሪያም ሆነ የተለመደ የአሰራር ተፈፃሚነት አይኖረዉም፡፡

**23.የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

ይህ መመሪያ በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት በጅምር ወይም በሂደት ላይ ያሉ መመሪያዉን የሚመለከቱ ጉዳዮች ካሉ በዚህ መመሪያ መሰረት ሊስተናገዱ ይችላሉ፡፡

## 24.መመሪያ ስለማሻሻል

ኤጀንሲው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን የአፈጻጸም መመሪያ በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሽል ይችላል፣

## 25.መመሪያው በስራ ላይ የሚውልበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅምንት ኤጀንሲ ኃላፊ ተፈርሞ ከወጣበት ከመጋቢት 21 ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ**
**መጋቢት 21 ቀን 2012 ዓ.ም**

**ጅሬኛ ሂርጳ ደበሎ**
**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራፊክ ማኔጅመንት አጀንሲ**
**ዋና ዳይሬክተር**